# ተሙዋጋች
# TEMUAGACH

በኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር የሚዘጋጅ

1ኛ ዓመት ቁጥር 10 ጥር 2000


## ርዕሰ አንቀጽ

### ለጠንካራ የፍትህ ሥርዓትና የሞያ ማኅበር

በአንድ አገር የፍትህ ሥርዓት ውስጥ የሕግ ባለሞያዎች እውቅ ሚና አላቸው:: የሕግ ባለሞያዎች ሰብአዊ መብቶችን፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኙትን መሠረታዊ የሰው ልጆችን መብቶች በማወቅ በኩል ተገቢ ንቃተ-ሕግ፣ ትምህርትና ሥልጠና ያላቸው በመሆኑ በተለይ ሕጋዊነትን (rule of Law) በማስፈን በኩል እንደታላቅ ባለድርሻ ይቆጠራሉ:: በዚህም ምክንያት አንዱና ዋነኛው ኃላፊነታቸው ሙያቸውንና የፍትህ ሥርዓቱን በማጠናከርና ሕጋዊነትን በማስከበር የሚጫወቱት ሚና ነው::

የሕግ ባለሞያዎች ይህንን ኃላፊነት መወጣት የሚችሉት ግን ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች መሟላት ሲችሉ ነው:: የመጀመሪያው አስፈላጊ ሁኔታ በነፃነት መደራጀት ነው:: መደራጀት ከሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶች አንዱ በመሆኑ፣ ጠበቆችም እንደዜግነታቸው ይህ መብት ስላላቸው በአባላቱ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሙያ ማኅበር እንዲኖራቸው የግድ ነው::

በዚህ እትም ስለሕግ ሞያተኞች፣ በተለይም ስለጠበቆች መሠረታዊ መርሆዎች በሰፈረው ጽሑፍ (ገጽ 2 ይመልከቱ) እንደተመለከተው ጠበቆች ማኅበሮቻቸው ለጥቅሞቻቸው እንዲቆሙላቸው፣ በሥልጠና አማካይነት የዕውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፉላቸው፣ የሞያ ክብራቸውን እንዲ ጠብቁላቸው፣ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ማኅበር በነፃነት የማቋቋምና ያለማንም ተጽዕኖ የዚሁ ማኅበር አባል የመሆን መብት አላቸው:: የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አካላትም በአባላት በተመረጡ ግለሰቦች የሚቋቋሙ ሆነው ሥራቸውን ያለአንዳች ጣልቃ ገብነት የሚያከናውኑ መሆን ይገባቸዋል::

የሕግ ባለሞያዎችን ሚና በሚመለከት በሰፈረው ጽሑፍ ውስጥ በመንግሥታት ላይ የተጣሉ ግዴታዎች ሁለተኛ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው:: ከእነዚህ የመንግሥት ግዴታዎች መካከልም ለጠበቆች ጉዳይ ትኩረት የመስጠትና ለማኅበራቸው ድጋፍ የማድረግ፣ ስለጠበቆች ሚናና ኃላፊነት ሕዝብ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖረው የማስቻል፣ ዜጎች ተገቢው የሥልጠና ደረጃ ባላቸው ጠበቆች የሕግ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣ ይህም መብት ያላቸው መሆኑን ለዜጎች የማሳወቅ ግዴታዎች ጥቂቶቹ ናቸው::

በሦስተኛ ደረጃ የሕግ ባለሞያዎችን በማፍራት ሚና ላይ የተሰማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቀ ሥልጠና በመስጠት ቢተጉ፣ በሥነ-ምግባር የታነፀ የሕግ ባለሞያ ቢያፈሩ ለሕብረተሰቡና ለግለሰቦችም የሚሰጠው አገልግሎት ጥራት ያለው እንደሚሆን ይታመናል። የሕግ ሞያ የሰውን ልጅ መሠረታዊ መብት፣ የሰውን ልጅ ክብር ሕይወት፣ የንብረት ባለቤትነትን በተመለከተ ክርክርና ውሣኔ የሚሰጥበት መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ጥራት ያለው ሥልጠና ጥራት ላለው አገልግሎት ወሳኝ ነው::

ከየኃላፊነታቸው አንፃር መንግሥታት፣ የጠበቆች የሌሎች የሕግ ሞያ ማህበራትም ሆነ የትምህርት ተቋማት ሊያስታውሱት የሚገባ ቁም ነገርም አለ። ይኸውም በሕግ ሙያ ተሠማርቶ ለመሥራት የዘር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የሌላ አስተሳሰብ ልዩነት ፈጽሞ የማይደረግ መሆኑን ነው:: ከላይ የጠቀስናቸው ሦስቱም ወገኖች ይህ ተግባራዊ መሆኑን ለመቆጣጠር ተግተው መሥራት አለባቸው::

ከዚህ በላይ በገለጽናቸው ሀሳቦች መሠረት ሁሉም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን ቢወጡ በዚህች አገር ጠንካራ የሕግ ሞያና ጠንካራ ማኅበር እንደሚኖር፣ ይህም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት፣ ለሕጋዊነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል::

## የጠበቆች ማኅበር ዓመታዊ ጉባኤውን አካሄደ

የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር የ1999 ዓመታዊ ስብሰባውን ከላንቻ በስተጀርባ በሚገኘው የማኅበሩ የተከታታይ የሕግ ትምህርት ማዕከልና የጠበቆች ክበብ ውስጥ በቅርቡ አካሄደ::

በዚሁ ስብሰባ ላይ የሥራ አሥፈፃሚ፣ የማኅበሩ ተቆጣጣሪዎችና የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርቶች ተደምጠው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በአባላት ጸድቀዋል:: ስብሰባውም ከመጠናቀቁ በፊት በቀድሞ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ውስጥ ላገለገሉ አምስት አባላት የምሥክር ወረቀት አሰጣጥ ሥነ - ሥርዓት ተካሂዷል::

### የማኅበሩ የተከታታይ ትምህርት ማዕከልና የጠበቆች ክበብ ሥራ ጀመረ

የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር የተከታታይ የሕግ ትምህርት ማዕከልና የጠበቆች ክበብ ተከፍቶ ሥራ ጀመረ::

የትምህርት ማዕከሉ ማህበሩ የአባላት ንቃተ-ሕግ ከጊዜ ወደጊዜ እየጐለበተ እንዲሄድ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥበት ሲሆን ክበቡ ደግሞ አባላት

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በፍርድ ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ወርክሾፕ ተካሄደ

የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራምና በወቅቱ የፍርድ ቤቶች ሁኔታ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ የቀረበበት ወርክሾፕ በተከታታይ የሕግ ትምህርት ማዕከልና በጠበቆች ክበብ ውስጥ በቅርቡ አካሄደ::

ይኸው ጥናታዊ ጽሑፍ ከቀረበ በኋላ ውይይት ተደርጐ ፍሬያማ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን ጥያቄዎች ቀርበው ተገቢ መልስ ተሰጥቶባቸዋል::

በመጨረሻም ጥናታዊ ጽሑፉን ለማዳበር ታዳሚዎቹ አስተያየቶቻቸውን በጽሑፍ አስፍረው ለአቅራቢዎቹ እንዲሰጡ በመስማማት ወርክ ሾፑ ተጠናቋል::

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ መጽሐፍ አሳተመ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ «የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች የመረጃ ሰነድ» የተባለውን መጽሐፍ አሳትሞ በማሰራጨት ላይ ነው::

ይኸው ሰነድ (Fact Sheet) በዋናነት እንዲደርስ የተፈለገው ለመንግሥታት፣

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ወቅታዊ ጉዳይ

# የጠበቆች ሚና መሠረታዊ መርሆዎች

*(ወንጀልን ስመከላከልና ስወንጀለኞችም መደ ረግ ስለሚገባው አያያዝ በስምንተኛው የተ ባበረት መንግሥታት ድርጅት ጉባኤ የፀደቀ ኦገስት 27- ሰፕቴምበር 1990 ሀቫና፣ ኩባ)*

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር መሠረት የዓለም ሕዝቦች ፍትህ የሚረጋገጥባቸውን ሁኔታዎች ለመፍጠር ቁርጠኝነታቸውን ያረጋገጡ ከመሆኑም በላይ ሰብዓዊ መብቶቹና መሠረታዊ ነፃነቶቹ ያለአንዳች የዘር፣ የፆታ፣ የቋንቋ ወይም የሃይማኖት ልዩነት መከበርና መጐልበት ለዓለም አቀፍ ትብብር አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታወቃል።

በዓለም ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ በሕግ ፊት ሁሉም ሰው እኩል መሆኑን፣ በሕግ ጥፋተኝነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ማንም ሰው ንጹህ ሰው ስለመሆኑ፣ ያልተዛባና ግልጽ የሆነ ፍትህን የማግኘት መብትና ኢያንዳንዱ በወንጀል የተ ከሰሰ ሰው ስለሚኖረው አስፈላጊ የዋስትና መርሆዎች ተቀም ጠዋል።

ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት ሰዎች ብቃት ባለው፣ ነፃና አድሎአዊ ባልሆነ ፍርድ ቤት ያለአንዳች መዘግየት የፍርድ ውሣኔ፣ የተስተካከለና ግልጽ ዳኝነትን የማግኘት መብታቸውን አውቆላቸዋል።

የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባሕላዊ መብቶች የዓለም አቀፍ ስምምነት መንግሥታት ሰብአዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ማስፋፋት፣ ማክበር፣ ማስከበር ቻርተሩ የጣለባቸው ግዴታ መሆኑን ይጠቁማል።

በጥበቃና በእሥር ላይ ለሚገኙ ሰዎች ከለላ የሚያደርገው የመርሆዎች ክፍል ያልተፈረደባቸው ሰዎች ድጋፍ የማግ ኘት መብት እንዳላቸው፣ በሚስጢርም ከሕግ አማካሪዎቻ ቸው ጋር እንዲገናኙና እንዲመካከሩም መብታቸው ይረጋ ገጣላቸዋል።

የሞት ቅጣትን ለሚጠባበቁ፣ ማንኛውም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 በሁሉም የፍርድ ሂደት ዕር ከኖች ሁሉ በቂ የሕግ ድጋፍ ሊሠጠው እንደሚገባ ያረጋግጣል።

የወንጀልና የሥልጣን ብልግና ሰለባዎች ፍትህ የማግኘት መብት እንዲኖራቸው፣ መልካም ኢያያዝ እንዲደረግላቸው፣ ካሣና አንዳንድ ክፍያዎችንም እንዲያገኙ ያሳስባል።

ሰዎች ሁሉ ለበቂ የሰብአዊ መብት ጥበቃና ለመሠረታዊ ነፃነቶች መጠበቅ መብት፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ የባህል ወይም የሲቪልና የፖለቲካ ሰውነት እንዲኖራቸው፣ ሰዎች ሁሉ ነፃ በሆነ የሕግ ባለሞያ በቂ የሕግ አገልግሎት ያገኙ ዘንድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል።

የጠበቆች ማኅበራት የሙያ ሥነ-ምግባርን የማስከበር፣ አባላቱንም ከእንግልት፣ አግባብነት ከሌለው ክልከላና የሕግ ጥሰት የመከላከል፣ የሕግ አገልግሎት ለሚፈልጉ ሁሉ አገልግሎቱን መስጠትና ከመንግሥትና ከሌሎችም ተቋማት ጋር በመተባበር የፍትህን አፈጻጸም ሁኔታና የሕዝብን ጥቅም የመጠበቅ ቁልፍ ሚና አላቸው።

የጠበቆችን ሚና በሚመለከት መሠረታዊ መርሆዎች የተቀረጹት አባል ሀገራት አግባብነት ያለውን የጠበቆች ሚና የማስፋፋትና እውን የማድረግ ተግባራቸውን ለመደገፍ ነው። ይህም ከበሬታ የሚቸረው ጉዳይ ነው። መንግሥታት በሕግ ማዕቀፋቸው ውስጥ ለጠበቆች ጉዳይ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ሌሎች ወገኖችንም አቃብያና ሕግ፣ አስፈጻሚዎች፣ ሕግ አውጭዎችና ጠቅላላ የሕዝቡም ትኩረት መስጠት አለበት። እነዚህ መርሆች የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖራቸው በሕግ ሞያ ላይ ተሠማርተው የሚሠ ሩትንም ይመለከታል።

### የጥብቅናና የሕግ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት፣

1. ሰዎች ሁሉ እራሳቸው በመረጧቸው ጠበቆች የሕግ ድጋፍ የማግኘት፣ ጠበቆች በሁሉም የወንጀል ክርክር ዕርከን ሂደት ላይ ጥበቃ እንዲያደርጉላቸው፣ እንዲቆሙላቸውና መብቶቻ ቸውንም እንዲያስከብሩላቸው መብት አላቸው።
2. የዘር፣ የቀለም፣ የጐሣ መሠረት፣ የፆታ፣ የቋንቋ የሃይማኖት የፖለቲካ እንዲሁም የማኅበራዊ መሠረት፣ የኢኮኖሚና የሌ ሎች ሁኔታዎች ልዩነት እንዳይደረግባቸው መንግሥታት ሰዎች ሁሉ የጠበቆች ተደራሽነት እንዲኖራቸው ብቃት ያለው ሥርዓትና የሚያሠራ ሁኔታ በየግዛተ ክልሎቻቸው መኖሩን ያረጋግጣሉ።
3. መንግሥታት ድሆችና ለሌሎችም ነዳያን እንደየአስፈላጊነቱ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኙ በቂ ገንዘብና ሀብት መመደቡን ያረጋግጣሉ። የጠበቆች ማህበራትም የሕግ ድጋፍ በመስጠትና በማደራጀቱ ረገድ መተባበር ይኖርባቸዋል።
4. መንግሥትና የጠበቆች ሙያ ማኅበራት በሕግ ውስጥ ስላላቸው መብትና ግዴታዎቻቸው፤ መሠረታዊ መብቶቻ ቸው እንዲጠበቁ ጠበቆች ስለሚጫወቱት ሚና ሕዝቡን

(ወደ ገፅ 3 ዞሯል)

የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር አምባሳደር፣ ኪዳኔ በየነ ሕንፃ፣ 1ኛ ፎቅ በሚገኘው ጽ/ቤቱ ውስጥ ባደራጀው ቤተ መጻሕፍታችን (የመረጃ ማዕከል) ይጠቀሙ። አባላት ዌብሳይታችንን በመጠቀም የጥብቅና አገልግሎታቸውን ማስተዋወቅ ይችላሉ።

የማኅበሩ ጽ/ቤት

ወቅታዊ ጉዳይ

## የጠበቆች ሚና. . .

(ከገፅ 2 የዞረ)

የማሳወቅ የግንዛቤ ፕሮግራም ያስ ፋፋሉ። ሙብቶቻቸውን እንዲያረጋግጡና እንደአስፈላጊነቱም የጠ በቆች እገዛ ያገኙ ዘንድ ለድሆችና ለሌሎችም ነዳያን የተ ለየ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

### በወንጀል ጉዳይ ልዩ ጥበቃ፣

5. ሰዎች ሁሉ በእሥርና ጥበቃ ላይ ባሉ ወይም በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ በመ ረጡት ጠበቃ ለመታገዝ መብት እንዳላቸው ለሚመለከታቸው የመን ግሥት ባለሥልጣናት ማሳወቃቸውን መንግሥታት ያረጋግጣሉ።
6. ጠበቃ የሌላቸው እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ሁሉ ለጠበቃ ለመክፈል ምንም አቅም ከሌላቸው ከጉዳያቸው ጋር ተመ ጣጣኝ የሆነ ልምድ ያለው ጠበቃ ተመ ድቦ የሕግ አገልግሎት ማግኘት ይኖርባቸዋል።
7. ሁሉም ሰዎች በወንጀል ወይም ያለ ወንጀል በታሠሩ ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ በታሠሩ በአርባ ስምንት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኙ መንግሥታት ያረጋግጣሉ።
8. ሁሉም ታሣሪዎች ወይም በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች ከጠበቆቻቸው ጋር ለመገናኘ ትና ለመመካከር እኩል የሆነ ዕድል፣ ጊዜና መገልገያ ይሰጣቸዋል። ይህም የሚሆነው ያለአንዳች መዘግየት፣ ያለ ጣልቃ ገብነትና ከሙሉ ምሥጢ ራዊነት ጋር ነው። ታሳሪ ዎች ከጠበቆቻቸው ጋር በሚገናኙበት ጊዜ የጥበቃ ኃይሎች በሩቅ ርቀት በዓይነ ቁራኛ ከመጠበቅ በቀር ታሳሪውና ጠበቃው የሚለዋወጡትን ሃሳብ መስማት የለባ ቸውም።

### የትምህርት ደረጃና ሥልጠና

9. መንግሥታት የጠበቆች ሙያ ማህበ ራትና የትምህርት ተቋማት የሕግ ባለሞ ያዎች ተገቢ እውቀትና ሥልጠና እንዲኖ ራቸውና ብሔራዊና ዓለም አቀፍ እውቅና ያለውን መልካም ነገርና የሕግ ባለሞያ ዎችን ሥነምግባራዊ ተግባራትና መሠረታዊ ነፃነቶችን ማወቃቸውን ያረጋግጣሉ።
10. መንግሥት የጠበቆች ሙያ ማህበ ራትና የትምህርት ተቋማት በሰዎች ላይ በዘራቸው፣ በቀለማቸው፣ በፆታ ቸው፣ በጐሣ መሠረታቸው፣ በኃይ ማኖታቸው በፖለቲካ ወይም በሌላ አስተሳሰብ፣ በብሔራቸውና ማኀበራዊ መሠረታቸው፣ በሀብታቸው፣ በውልደ ታቸው በኢኮኖሚ ወይም በሌላ ደረጃ በሕግ መስክ ገብቶ ለመሥራት ልዩነት የማይደረግባቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህም አባባል አንድ የሕግ ባለሞያ የአገሩ ዜጋ መሆን አለበት ከሚለው መርህ ጋር አይጋጭም።
11. ቡድኖች፣ ማኀበረሰቦችና ክልሎች የሕግ አገልግሎት ፍላጐታቸው ሳይሟ ላላቸው የቀረና፣ በተለይም የተለየ ባሕል፣ ወግ ወይም ቋንቋ አለዚያም ያለፈ መድልዎ ሰለባ ሆነው ሲገኙ መንግሥት፣ የጠበቆች ሙያ ማኀበ ራትና የትምህርት ተቋማት የእነዚህ ወገኖች እጩዎች ወደ ሕግ ሙያ ገብተው ለፍላጐታቸው ተስማሚ የሆነ ሥልጠና እንዲወስዱ እድሉ እንዲሰጣቸው የተለየ እርምጃ ይወስዳሉ።

### ግዴታና ኃላፊነት

12. ጠበቆች የፍትህ አስተዳደሩ ዓቢይ አካሎች እንደመሆናቸው መጠን ዘወ ትር የሙያቸውን ክብር ይጠብቃሉ።
13. ጠበቆች ለደምበኞቻቸው ያላቸው ተግባ ራት የሚከተሉትን ያካትታል፡-
    ሀ/ ከሙብትና ግዴታቸው ጋር እስከተ ዛመደ ድረስ ደንበኞቻቸውን ስለሕግ ሥርዓቱ አሠራር፣ ስለሙብቶቻ ቸውና ግዴታዎቻቸው ይመክራሉ።
    ለ/ ለደንበኞቻቸው በማንኛውም አግባብ በሆነ መንገድ ጥቅሞቻቸውን ለመጠ በቅ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስዱ ድጋፍ ይሰጣሉ።

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## የማህበሩ የተከታታይ. . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

በዕረፍት ጊዜያቸው እየተገናኙ ሙያዊ ውይይት የሚያካሂዱበት ነው። የክ በቡ መጀመር ለኢትዮጵያ ጠበቆች ማኀበርና ለአባላቱ ህብረት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር ወርክ ሾፖችንና ዓመታዊ ስብሰባዎችን የሚያካሂደው በዚህ የተከታታይ ትም ህርትና ክበብ ውስጥ ነው።

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ. . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

ባለሥልጣናት፣ ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድር ጅቶች፣ ለመንግሥታቱ ድርጅት ሠራተኞች፣ ለግሉ ዘርፍ ዋና ተዋ ናዮች (ድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖችን ጨምሮ) እና ለራሳቸው ለሰብአዊ ሙብት ተከላካዮች ነው።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ ሙብቶች ጉባኤ ይህን የሰነድ ሕትመት ተግባራዊ ለማድረግ የቻለው ኢኒሼቲቭ አፍሪካ ከተባለው አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

**ተሚጋች** - በኢትዮጵያ ጠበቆች ማኀበር በየሁለት ወር የሚታተም

ስልክ : 251-11-553-0122
ፖ.ሣ.ቁ. : 700
ፋክስ : 251-11-515-2047
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢ.ሜይል : eba@ethionet.et
ዌብሳይት : www.ethiopian-bar.org

ወቅታዊ ጉዳይ

## የጠበቆች ሚና. . .

(ከገፅ 3 የዞረ)

ሐ/ በፍርድ ቤት፣ በልዩ ፍርድ ቤት ወይም በባለሥልጣናት ፊትና አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ለደምበኞቻቸው ድጋፍ ይሰጣሉ።

14. ጠበቆች የደምበኞቻቸውን መብቶች ለማስጠበቅና ፍትህንም ለማስፋፋት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት በብሔ ራዊና በዓለም አቀፍ ሕግ እውቅና የተሰጣቸውን ሰብአዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶች መጠበቅና ማክበር ይኖርባቸዋል። በሕግ መሠረት በሚታወቁትና ደረጃ ቸውን ባሟሉ ሙያዊ የሕግ ሥነ-ምግባሮች ይመራሉ።

15. ጠበቆች የደምበኞቻቸውን ጥቅሞች ዘወትር በታማኝነት ያከብራሉ።

### ለጠበቆች ተግባር ዋስትናዎች፣

16. መንግሥታት ጠበቆች:-

ሀ/ የሙያ ተግባራቸውን ያለፍራቻ፣ መሰናክል፣ ወከባ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ማከናወን መቻላቸውን ያረጋግጣሉ።

ለ/ በአገራቸው ውስጥና ውጭም ተጉዘው ከደምበኞቻ ቸው ጋር በነፃነት እንዲመካከሩ ያደርጋሉ።

ሐ/ በታወቁና የሙያ ሥራ ደረጃቸውን በጠበቁ ሥነ ምግባራት በተከናወኑ ተግባራት ሁሉ ስቃይ ወይም የአስተዳደር እንግልት፣ ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ማዕቀቦች እንዳይደርስባቸው ይጠብቃሉ።

17. ጠበቆች ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ደህንነታቸው ሥጋት ላይ የወደቀ እንደሆነ ባለሥልጣኖች በቂ ጥበቃ ያደርጉላቸዋል።

18. ጠበቆች ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ሂደት ላይ ከደም በኞቻቸው ጉዳይ ጋር መፈረጅ የለባቸውም።

19. አንድ ጠበቃ የጥብቅና ፈቃዱ ካልተሠረዘ በቀር ፍርድ ቤቶችና የአስተዳደር ባለሥልጣናት በአገሩ ሕግ አሠራርና በነዚህም መርሆዎች መሠረት ጠበቃው በሕግ ፊት ለደምበኛው እንዳይቆም መከልከል አይቻላቸውም።

20. ጠበቆች በፍርድ ቤት፣ በልዩ ፍርድ ቤት ወይም በሕግና የአስተዳደር ባለሥልጣኖች በፊት ሲቀርቡ በጽሑፍም ሆነ በቃል በቅንነት ለሰጧቸው ሀሳቦች የፍትሐብሔርና የወንጀል ተጠያቂነት እንዳይኖርባቸው ከለላ አላቸው።

21. ጠበቆች ለደምበኞቻቸው ውጤታማ የሚሆን የሕግ እገዛ መስጠት ይችሉ ዘንድ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት በእጃቸው ያሉ ወይም በኃላፊነት የያዟቸውን ጠቃሚ መረጃዎች፣ ፋይሎችና ሰነዶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ግዴታቸው ነው። እንደዚህ ያለው መብት ተግ ባራዊ መሆን ያለበት አንዳች ጊዜ ሳይወስድ ነው።

22. መንግሥታት በጠበቆችና በደምበኞቻቸው መካከል ለሚደረጉ ግንኙነቶችና ምክክሮች እውቅናና ከበሬታ ይሠጣሉ።

### የመናገርና በማኀበር የመደራጀት ነፃነት፣

23. ጠበቆች እንደሌሎች ዜጐች ሁሉ የመናገር፣ የዕምነት፣ በማኀበር የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነት አላቸው። በተ ለይም ሕግን፣ የፍትህ አስተዳደርንና ሰብአዊ መብት ጥበቃና ሀሳቡን ማስፋፋትን በሚመለከቱ ሕዝባዊ ውይይቶች ተሳታፊ ይሆናሉ። ሕጋዊ በመሆናቸውና በሕጋዊ ማኀበር በመታቀፋቸው አንዳች ስቃይና እንግልት ሳይደርስባቸው የአካባቢ፣ የብሔራዊና የዓለም አቀፍ ማህበራት አባላት ሊሆኑ ይችላሉ።

### የጠበቆች ሙያዊ ማህበራት፣

24. ጠበቆች ለጥቅሞቻቸው እንዲቆሙላቸው፣ ትምህርታቸውና ሥልጣናቸው እንዲስፋፋላቸውና የሞያቸው ክብር እንዲጠበቅ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ማኀበር የማቋቋምና አባልም የመሆን መብት አላቸው። የማኀበራቱ ሥራ አስፈፃሚ አካላትም በአባላቱ የሚመረጡ ሆነው ሥራቸውን ያለአንዳች ጣልቃ ገብነት የሚያከናውኑ ይሆናሉ።

25. የጠበቆች ሙያ ማህበራት ማንም ሰው ውጤታማና እኩል የሆነ የሕግ አልግሎት እንዲያገኝና ያለአንዳች ጣልቃ ገብነት በሕግ አግባብ፣ በታወቀ የሙያ ደረጃና ሥነ ምግባር ደምበኞ ቻቸውን ለመምከርና ድጋፍ ለመስጠት እንዲችሉ ከመንግሥት ጋር ይተባበራሉ።

### የዲሲፕሊን ሂደቶች፣

26. የጠበቆችና የሙያ ሥነ ምግባራት ብሔራዊ ሕግና ባሕልን፣ እውቅና ያለውን ዓለም አቀፍ ደረጃና ልምድን መሠረት በማድረግ በሕግ ሙያና አግባብነት ባላቸው አካላቱ የሚመሠ ረት ይሆናል።

27. በጠበቆች ላይ ከጥብቅና ሥራቸው ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎች ሚዛናዊ በሆነ ትክክለኛ ሂደት በፍጥነት ያታያሉ። ይህም ሲሆን ጠበቆች እራሳቸው በመረጡት ጠበቃ መታገዝን ጨምሮ በሚዛናዊነት የመስማት መብት ይኖራቸዋል።

28. በጠበቆች ላይ የሚጀመሩ የዲሲፕሊን እርምጃ ሂደቶች የሚቀርቡት ከአድልኦ የፀዳና በሕግ ባለሞያዎች በተቋቋመ የዲሲፒሊን ኮሚቴ ወይም ነፃና ሕጋዊ ሥልጣን ባለው አካልና ፍርድ ቤት ፊት ነው። ይህም ነፃ በሆነ ዳኝነት እንደገና ሊታይ ይችላል።

29. ሁሉም የዲሲፒሊን ጉዳዮች የሚወሰኑት በሙያው ሥነ ምግባርና በሌሎች እውቅና በተሰጣቸው ሕጐችና መርሆዎች መሠረት ነው።

# የዳኝነት ሥርዓቱ

*ይህ ተከታዩ ጽሑፍ «አጠቃላይ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ሪፖርት» በሚል ርዕስ በአቅም ግምባታ ሚኒስቴር የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ጽ/ቤት ካጠናቀረው ጥናት የተወሰደ ነው።*

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ፍርድ ቤቶችን የሚመለከት ሲሆን የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች እንደሚቋቋሙ ይገልፃል። ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች፣ በተጓዳኝም ለባሕላዊና ለኃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ሕገ - መንግሥቱ ዕውቅና ይሰጣል። በሕገ-መንግሥቱ ባይገለጽም ማኅበራዊ ፍ/ቤቶችም አሉ። በማህበራዊ ፍ/ቤቶች በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ ወደ ክልል ፍ/ቤት ይግባኝ የሚፈቅድ ሥነ - ሥርዓትም አለ። ይሁንና ማኅበራዊ ፍ/ቤቶችን በተመለከተ ያለው አሠራር በሁሉም ክልል ወጥ አይደለም። በፌዴራል ደረጃ የፍርድ ቤት ዳኞች ምርጫ፣ የአገልግሎት ሁኔታ፣ ዲሲፕሊንና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች የሚመለከተው የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ነው። በክልል መንግሥታት ያሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤዎችም ተ መሳሳይ ተግባራትን ያከናውናሉ።

የኢትዮጵያ የፍትህ ሥርዓት በመሠረቱ ሦስት ዋና ዋና ችግሮች አሉበት። አንደኛ በቀላሉ ተደራሽ አለመሆንና ለዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ፍላጐት ምላሽ የሚሰጥ አለመሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛ የፍትህ አስተዳደሩ ሙስናን፣ በሥልጣን አላግባብ መገልገልና ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነትን በማስወገድ ረገድ ገና ብዙ ጠንካራ እርምጃዎች መወሰድ ያለባቸው መሆኑንና በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ለፍትህ አስተዳደሩ የሚመደበው ገንዘብ አነስተኛ መሆኑና ይህም ያለውን ዝቅተኛ አፈፃፀም የሚያባብስ ሆኖ መገኘቱ ናቸው።

በፍርድ ቤቶች ነፃነት ላይ በሕዝቡ ዘንድ ያለው እምነት በጣም ዝቅተኛ ነው። በፌዴራልም ሆነ በክልል የፍርድ ቤቶችን የዕለት ተዕለት ሥራ የመምራትና መቆጣጠር ሥራ የፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች ኃላፊነት ነው። በመሆኑም የፍ/ቤት ፕሬዚዳንቶች የዳኝነትም ሆነ የአስተዳደር ሥራን ደርበው የሚሠሩ ናቸው። ተጠሪነታቸውም ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ፕሬዚ ዳንት ነው። ይህ አሠራር ነፃነታቸውን ሊጐዳ የሚችል ነው። የዳኞች ምርጫና እድገት የሚፈፀምበት አሠራርም በሚገባ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ የሕግ ሞያተኞችን ተሳትፎ የሚጋብዝ አይደለም። የአፈ ፃፀም ምዘናውም ቢሆን ተመሳሳይ ነው።

የዳኞች ሥልጠና ሥርዓት አለመኖር የኢትዮጵያን የዳኝነት ሥርዓት አንዱ ዋነኛ ችግር ነው። የፍ/ ቤቶች አስተዳደርና የጉዳዮች አያያዝም ደካማ ነው። እያንዳንዱ ዳኛ በአማካይ የሚያየው ጉዳይ ባለፉት አመታት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። ሁሉንም ዓይነት ሕጋዊ መረጃዎች በቀላሉ የማግኘቱ ጉዳይም ውሱን ነው። ፍ/ቤቶች የወጡ ሕጐችን በቀላሉ አያገኙም። አብዛኞዎቹ ፍ/ቤቶች ቤተ መጻሕፍት የላቸውም። ቢኖሩም በአግባቡ የተደራጁ አይደሉም። አብዛኞዎቹ የፍ/ቤት ውሣኔዎችም አይታተሙም። ምንም እንኳን ፍ/ቤቶች አለመ ግባባቶችን ለመፍታት ተገቢ ተቋማት መሆናቸውን ሕብረተሰቡ ቢገነዘብም ስለፍ/ቤት አሠራር ሥነ - ሥርዓት ማወቅ የሚችሉ ፍ/ቤት ጉዳይ ያላቸው ብቻ ናቸው። ዳኞች የሚገኙበት ተስማሚ ያልሆነ የሥራ ሁኔታ ነፃነታቸውን የሚጋፋ፣ የሥራ ቅልፍጥናቸውን የሚቀንስና ለሙስና የሚጋብዝ ነው።

# የሀዘን መግለጫ

*በ1999 እና በ2000 ስድስት የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር አባላት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። እነርሱም፦*

*1ኛ/ አቶ ዓለሙ ፎክዮን*

*2ኛ/ » ስነ ቦጃ*

*3ኛ/ » ደጀኔ ሺፈራው*

*4ኛ/ » ሰሎሞን ዓለማየሁ*

*5ኛ/ » አሰፋ ደምሴ*

*6ኛ/ » አበራ ወልደዮሐንስ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ይመኛል።*

ይህ እትም ለንባብ የበቃው በኢኒሼቲብ አፍሪካ በኩል ከስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።